## ልደተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

**“ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል”(ኢሳ 9፡6)**

በመጀመርያ እግዚአብሔር ባሕርይው እያመሰገነው ብቻውን ይኖር ነበር እርሱ ብቻውን ቀዳማዊ ነው ፣ ብቻውን ሕይወት ነው ፣ እርሱ ብቻውንም ፍቅር ነው፣ እርሱ በዘመናት የሸመገለ ነው። የፍቅሩ መገለጫ ይሆን ዘንድ ሁሉን ቻዩ ጌታ የእርሱ የባሕርይው የሆነውን ሕይወት በጸጋ ይወርሱ ዘንድ በ6 ቀናት 22 ፍጥረታትን ፈጠረ። 22ኛው ፍጥረት ግን ከሁሉም ፍጥረታት የተለየ ነበር ፣ ከሁሉም ፍጥረታት ተለይቶ ቀድሞ ከእርሱ በፊት የተፈጠሩትን ፍጥረታት ሁሉ ይገዛ ዘንድ ሥልጣን ተሰጠው ፣ በአምላኩ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ተፈጥሯልና እንደ አምላኩ ገዢ ሆነ። እግዚአብሔር ገዢነቱ በባሕርይ ነው እንጂ ማንም አልሰጠውም ፣ ነገር ግን እርሱ በባሕርይ ፍቅር ስለሆነ የእርሱ የሆነውን ሁሉ በጸጋ ለ22ኛው ፍጥረት ለሰው ሰጠው፣ ሰውም ገዢነቱ የተሰጠው እንጂ ከእርሱ አንዳልሆነ ያውቅ ዘንድ ፣ ያለው ነገር ሁሉ “አትብላ” የሚለውን ትእዛዝ እስከጠበቀ እንደሚጠበቅለት አምላኩ እግዚአብሔር አስታወቀው።

ሰውም በሁሉም ነገር ላይ ገዢ ላደረገው ለእግዚአብሔር ከመገዛት ይልቅ ፣ የኃጢአት ተገዢ ሆነ “አትብላ” የተባለውን ትእዛዝ አፈረሰ ፣ ሟችና በምድርም ተቅበዥባዥ ሆነ ፣ የአምላኩን የእግዚአብሔርን መልክም አጣ። በዚህ ጊዜ ወደ አምላኩ ለመነ የልብን ጩኸት የሚሰማ እግዚአብሔርም ልመናውን ሰማው “ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንኃለው” ብሎ የተስፋ ቃልንም ሰጠው።

ሰውም ይሄን የተስፋ ቃል ይዞ ጥበቃውን ጀመረ ያ ሕይወት የሚሆነውን፣ የጨለማን ኃይል የሚያፈርሰውን መድኃኒት እስኪወለድ ሴት ልጁን እያየ ጥበቃውን ጀመረ፣ አንድ ፣ ሁለት ፣ ሦስት እያለ አምስት ቀን ሞላ ፣ ከዚያም አልፎ ስድስት ፣ ሰባት ፣ ስምንት ብሎ አሥር ሞላ ነገር ግን ያ የጠበቀው መድኃኒት የውኃ ሽታ ሆኖ ቀረ። እግዚአብሔር ረስቶ ይሆን? ፣ ዘግይቶ ይሆን?፣ ቃሉን ሽሮ ይሆን? በፍጹም እንዲያ አይደለም እግዚአሔር ቃሉን ያጥፍ፣ ይዘገይ ዘንድ ሰው አይደለም ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ቀን አንድ ሺህ ዓመት መሆኑን ሰው ረሳ እንጂ። እንዲህ እያለ ሺህ ዓመታት ተቆጠሩ ፣ ብዙ ነቢያትም ይህ የሚወለደውን መድኃኒት በትንቢት መነጽር አይተው ስለእርሱ ተነበዩ ። ኢሳይያስ “ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።” አለ ሚክያስም “አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።” አለ ሌሎች ነቢያትም ይህን መድኃኒታቸውን በትንቢት አይተው ነገር ግን በአይናቸው ሳሳዩት በተስፋ በልባቸው አኑረውት አለፉ።

የቀጠሮውን ቀን የማይዘነጋ እግዚአብሔርም የአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ አንዲት ሰከንድ እንኳን ሳታልፍ አካላዊ ቃል ልጁን በመልአኩ ገብርኤል በኩል ናዝሬት ገሊላ ውስጥ ወደ ምትገኝ ወደ አንዲት ድንግል ዘንድ ላከ ። ይህቺ ድንግል በአባቷ ከንጉሱ ከዳዊት ወገን ብትሆንም ያን ጊዜ እሥራኤል በሮም ቅኝ ግዛት ስር ስለነበረች ምንም ያልነበራት ደሃ ነበረች። እግዚአብሔር ግን ከነገስታት ፣ ከመኳንት እና ከሃብታሞች ይልቅ ፣ የድንግልን ውበት ወደደ ፣ አንድያ ልጁን ወደእርሷ ሰደደ እርሷም “እነሆ ባርያህ” ብላ አምላኳን በማኅጸኗ ተቀበለች። ዘጠኝ ወር በሞላት ጊዜም የህዝብ ቆጠራ ነበርና ከዮሴፍ ጋር ትቆጠር ዘንድ ወደ ቤተልሔም ወረደች።

ድንግሊቱም ልጇን ልትወልድ ደርሳ እንግዳ ማረፍያ ፍለጋ በቤተልሔም ተዛወረች ነገር ግን የዓለማትን ፈጠሪ በሆድዋ ይዛ ለእርሷ የሚሆን ማረፍያ አጣች። የተገኘላት አንድ ቦታ በከብቶች በረት ሆነ ፣ በበረት ውስጥም ያን ነቢያት የጠበቁትን መድኃኒት ፣ ፈጣሪዋን ወለደችው ። ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በሰው ላይ የነገሰን የዲያብሎስን ፍላጻ ያስወግድ ዘንድ የዓለማት ፈጣሪ በበረት ውስጥ ተኛ ፣ እምባን የሚያብስ ያዘኑትን የሚያረጋጋ አምላክ እንደ ሕፃናት አለቀሰ ፣ ፍጥረታትን ሁሉ የሚያለብስ ጌታ ፣ በጨርቅ ተጠቀለለ እንስሳትም በትንፋሻቸው አሞቁት።



እረኞችም ከመላእክት ጋር ሆነው “በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን በምድር ለሰው ልጅ ሰላም በዛሬው እለት በዳዊት ከተማ መድኃኒት ተወልዷልና” እያሉ አመሰገኑት። እኛም ከኢሳይያስ ቃልን ተውሰን በደስታ እንዲህ እንላለን ““ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል”።

ልደት የተስፋ፣ የፍቅር እና የመቤዠት ተስፋ ምልክት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር እና ኢየሱስ ወደ ዓለም ያመጣውን የፍቅርና የሰላም መልእክት የሚያስታውስ ነው።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ስለ ልደት ባስተማረው ትምህርቱ ላይ እንዲህ ይላል፡

“በወንጌል ዘገባ ወደ ቤተልሔም እንሂድ። በእውነት እረኞች ከሆንን እና መንጎቻችንን የምንጠብቅ ከሆነ፣ ይህን ታላቅ ደስታ የምስራች የሚያውጅ የመላእክቱ ድምፅ ወደእኛ በእርግጥ ቀርቧል። እንግዲያው፣ ወደ ሰማያዊ ሠራዊት እንመልከት፣ የመላእክት ማኅበርን እንይ፣ እናም መለኮታዊ ዝማሬያቸውን እንስማ። ድግሱን የሚያከብሩስ ድምፅ ምንድር ነው? " ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን " እያሉ ይጮኻሉ። መላእክቱ በአርያም ያለውን መለኮትነት ያከብራሉን? ብንል እነርሱስ "በምድርም ሰላም" ይላሉ. መላእክት በታላቅ ትዕይንት እጅግ ደስተኞች ሆነዋል፡ "በምድርም ሰላም"። ቀደም ሲል የተረገመው፣ እሾህና አሜከላን ያፈራ፣ የግጭት ቦታ፣

የተፈረደበት ምርኮኛ፣ ሰላም አግኝቷል። ኸረ ይገርማል! "እውነት ከምድር ወጣች ጽድቅም ከሰማይ አየች።" የሰው ምድር ያፈራችው ፍሬ እንዲህ ነው። እነዚህም ነገሮች የሚፈጸሙት የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ለሰው ልጆች ስለሆነ ነው። የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ከፍታ ከፍ እንዲል እግዚአብሔር ከሰው ተፈጥሮ ጋር ተዋሕዷል። ይህንንም ዜና ከሰማን በኋላ ወደ ቤተ ልሔም እንሂድና ይህንን ድንቅ ተአምር እንይ ድንግል በመውለዷ እንዴት ሐሴት እንደምታደርግ፣ ጋብቻን የማታውቅ ሕፃንዋን እንዴት እንደምታጠባ አዲሱን ትዕይንት እንይ። “

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ይሄንን ደስታ እንዲህ ባለ ቃል ያመሰግናል፡

“ጀሮዎቼ የእረኞችን መዝሙር ያደምጣሉ፣  ድምጹ ያነሰ ዜማ አያቀርቡም፣ ነገር ግን ሙሉ ሰማያዊ መዝሙር ይዘምራሉ እንጂ። ቅዱሳን መላእክት ይዘምራሉ፣  ሊቃነ መላእክት ድምፃቸውን በአንድነት ያዋሕዳሉ። ኪሩቤል የደስታ ውዳሴአቸውን ይዘምራሉ። ሱራፌልም ክብሩን ከፍ ፣  ከፍ ያደርጋሉ። ሁላቸውም ተባብረው መለኮትን በምድር ፣ ሰውንም በሰማይ እያዩ ይህንን ቅዱስ በዓል ያመሰግናሉ። በላይ ያለው እርሱ አሁን ቤዛ ይሆነን ዘንድ በታች ሆኗልና ፤ የተዋረደውም በእግዚአብሔር ምሕረት ከፍ ከፍ ብሏልና። ”

የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የትህትና ልደት ነው እርሱ በምድር ካሉ ሴቶች ሁሉ ደሃዪቱን ወደደ ፣ ከቤተ መንግስት ይልቅ የከብቶች ግርግም ተመቸው ፣ ከብዙ አልባሳት ይልቅ የእንስሳት ትንፋሽ አሞቀው ስለዚህ ምን እንላለን? ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይሄን ታላቅ ምሥጢር ለመግለጽ ቃላት ቢያጥረው እንዲህ ብሏል“ ምን ልበል! እና ይህን ልደት እንዴት ልገልጽልላችሁ? ይህ ድንቅ ነገር በግርምት ይሞላልኛልና። በዘመናት የሸመገለው ሕፃን ሆነ። በላዩ እና በሰማያዊው ዙፋን ላይ የተቀመጠው አሁን በግርግም ተኝቷል። የማይነካውና ሊነካ የማይችለው፣ ቀላል፣ ውስብስብ እና አካል የሌለው፣ አሁን በሰው እጅ ተይዟል። የኃጢአተኞችን እስራት የሰበረ አሁን በሕፃንነት እስራት ታስሯል። ነገር ግን ውርደት ክብር እንዲሆነው፣ በስም መጥፋት ክብርን እንዲለብስ፣ የቸርነቱ መጠን ደግሞ ፍጹም ውርደት እንዲሆን ወስኗል።”

ስለዚህ የደስታ ቀን ምን እንላለን? ይህን ቀን ለማየት ሰው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ጠብቋልና ፣ ይሄን ቀን ለማየት ነቢያት ተመኝተው ነበርና ነገር ግን በትንቢት መነጽር አይተው ስለርሱ ትንቢት ተናግረው አልፈዋል። አባታችን ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ የነቢያት ትንቢት መፈጸሙን እንዲህ ባለ ምስጋና ያበስራል ” ይህ ቀን እነርሱን፣ ነቢያትን፣ ነገሥታትን እና ካህናትን ያስደሰተችበት ቀን ነው፣ ምክንያቱም ቃላቸው በእርሱ ተፈጽሞአልና፣ እናም ሁሉም በእውነት ተፈጽመዋል! ድንግል በዚህች ቀን አማኑኤልን በቤተ ልሔም ወልዳለችና። (ኢሳይያስ 10:19) የጥንት ኢሳይያስ የተናገረው ድምፅ ዛሬ እውን ሆነ። የአሕዛብን ቁጥር በጽሑፍ የሚናገር በዚያ ተወለደ። ዳዊት በአንድ ወቅት የዘመረው መዝሙረ ዳዊት ዛሬ ደርሷል! ሚክያስ በአንድ ወቅት የተናገረው ቃል፣ (ሚክያስ 5፡2) ዛሬ በእርግጥ ተፈጽሟል! አንድ እረኛ ከኤፍራታ መጥቶ ነበርና፥ በትሩም በነፍሶች ላይ ተወዛወዘ። እነሆ! ከያዕቆብ ኮከብን አበራ፣ (ዘኍልቍ 24፡17) ከእስራኤልም ራስ ተነሣ። (ሆሴዕ 1፡11) በለዓም የተናገረው ትንቢት ዛሬ ፍቺውን አገኘ! ወርዶ የተሰወረው ብርሃን መጣ፣ እናም ከአካሉ ውበቱ ወጥቷል! በዘካርያስ የተናገረው ብርሃን ዛሬ በቤተልሔም በራ! የመንግስት ብርሃን በኤፍራታ የንጉሥ ከተማ ተነሳ። ያዕቆብ የባረከው በረከት ዛሬ ተፈፀመ! ያም ዛፍ፣ የሕይወት ዛፍ፣ ለሟች ሰዎች ተስፋን ይሰጣል! የተደበቀው የሰሎሞን ምሳሌ( ምሳሌ 3፡18) ዛሬ ማብራሪያን አገኘ! ዛሬ ሕፃን ተወለደ ስሙም ድንቅ ተባለ! (ኢሳይያስ 9፡6) “

ይህን የተወለደውን ሕፃን ያዩ ዘንድ በኮከብ እየተመሩ ከሩቅ ምስራቅ ነገስታት እጅ መንሻ ወርቅ ፣ እጣን ፣ ከርቤ ይዘው መጡ እነርሱ ነገስታት ቢሆኑም ዝቅ ብለው በድንግሊቱ እቅፍ ውስጥ ላለው ሕፃን ሰገዱለት እርሱ ሰማያዊ ንጉስ ነውና ፣ ኮከብ አምላኪ የነበሩት ሰዎች በሚያመልኩት ኮከብ ወደ እውነተኛው አምላክ ተመሩ ስለዚህ ምሥጢር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይላል “እግዚአብሔር ጠቢባንን በሚያውቁት ነገር ጠራቸው፤ ኮከብ ቆጣሪዎች በመሆናቸው እንዲህ ባለው ትልቅ ኮከብ ተገርመዋልና። እግዚአብሔር ስሕተተኞችን ለማዳን ራሱን በኮከብ ቆጣሪዎች እንዲያገለግል እንደፈቀደ፣ በተለምዶ ዲያብሎስን እንዲያገለግል፣ ሰብአ ሰገልን ከልማዳቸው እንዲያርቅ እና ወደ ከፍተኛ ጥበብ እንዲመራቸው ፈቀደ”



እኒህ ነገስታትም መልአኩ በመጣችሁበት መንገድ አትመለሱ ባላቸው መሠረት ሕፃኑን በእናቱ እቅፍ ካገኙ በኋላ ወደ መጡበት ኮከብ ቆጠራ አልተመለሱም ፣ ለዘላለም የሚያበራ ኮከብን በቤተልሔም አግኝተዋልና ከዚህ በኋላ ሌላ ኮከብን በሰማይ መመልከት አላስፈለጋቸውም ናዛዜው ቅዱስ መክስምያኖስ ስለዚህ እንዲህ ይላል “ ፀሀይ በወጣች ጊዜ ዓይን ለከዋክብት ቸልተኛ እንደምትሆን ሁሉ አእምሮም ወሰን በሌለው የእግዚአብሔር ብርሃን ሲበራ በእርሱ ለተፈጠረው ነገር ሁሉ የማይሰማ ይሆናል። ሰብአ ሰገል ስጦታቸውን ብቻ ጥለው አልሄዱም፤ ምክንያቱም በልምዳቸው ለዘላለም የተለወጡ ሰዎች ሆነው ከክርስቶስ መገኘት ወጡ። እጅግ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ሁኔታ ውስጥ የተወለደ ትንሽ ልጅ በመገኘቱ የላቀ የማሰብ ችሎታቸው እና እውቀታቸው ግራ ተጋብቷልና።”

በእውነት እነሆ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት ተወልዶልናልና ሐሴትን እናድርግ።

እንኳን ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደርሰን አደረሳችሁ፣ መልካም በዓል ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር ይቆየን።

የጥቁር አንበሳ ግቢ ጉባኤ ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል።